# ወይ አብረን እንሳቅ ካልሆነም አብረን እናልቅስ! (ከይገርማል)

በየአካባቢው እየተደረጉ ያሉት ጸረ-ወያኔ እንቅስቃሴወች ክልላዊ ባህሪ መያዝ ያሳሰባቸው ግለሰቦች የሰሞኑ የአማራ እንቅስቃሴ የኢትዮጵያውያን እንጅ የአማሮች መባል የለበትም ብለው ሲከራከሩ እየተደመጡ ነው:: ከኢትዮጵያዊነት ደረጃው ዝቅ ብሎ የማያውቀው አማራ ዛሬ ላይ በአካባቢው የታጠረ የሚመስል ትግል እያደረገ መሆኑ ግልጽ ነው:: "ወልቃይት የአማራ ነው! በአማራ ላይ ያነጣጠረ የዘር ምንጠራ ይቁም! የወያኔ የበላይነት ይብቃ!---" እያለ ድምጹን ከፍ አድርጎ መፈክር እያሰማ ነው:: ይህን እንዲል ያስገደደው በራሱ ላይ ያነጣጠረ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ስለተከፈተበት እንደሆነ በበኩሌ እረዳለሁ:: በህልውናው ላይ የተጀመረውን የጥፋት ዘመቻ ለመመከት ደፋ ቀና እያለ ያለው አማራ የሌሎች ወገኖቹ ህይወት አሳስቦት በኦሮሚያና በሌሎች ክልሎች የሚፈጸመውን የወያኔ የዕብሪት ጭፍጨፋ እያወገዘ ኢትዮጵያዊነቱን ማስመስከሩም አልቀረም::

የአማራውን ትግል ፍጹም ኢትዮጵያዊ መልክ ለመስጠት የሚደረገው ሙከራ ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊያመዝን እንደሚችል መገንዘብ ተገቢ ነው:: የአማራው ትግል በሀገራችን እንደቅንጦት የሚታዩት የዴሞክራሲያዊ መብቶች ይከበሩ በማለት የሚደረግ ትግል ሳይሆን ከወያኔ የዘር ማጥፋት ዕቅድ ለማምለጥ የሚደረግ የሞት ሽረት ትግል ነው:: አማሮች በሰላም ከሚኖሩበት አካባቢ እየተለቀሙ ሲታረዱ አንድም ክልል ሀዘናቸውን የተጋራ፡ የተቃውሞ ድምጹን ያሰማ አልነበረም:: ወደፊት ጊዜ ፍንትው አድርጎ የሚያወጣው ሀቅ የሚጠበቅ ሆኖ አሁን ባለን ግርድፍ መረጃ መሰረት በግላጭ ከተገደሉት በተጨማሪ ሦስት ሚሊዮን ያህል አማራ ያርግ ወይ ይስረግ ሳይታወቅ ዳብዛው ጠፍቶ ቀርቷል:: ይህንን አማራ-ተኮር እልቂት ሲያቀነባብሩ ከነበሩት ወያኔወች ጎን በመሰለፍ የአማራ ወኪል ነኝ የሚለውን ብአዴንን ጨምሮ ሁሉም ክልሎች በአማሮች ላይ የተለያየ የግፍ አይነት ፈጽመዋል:: ዛሬ ላይ እኒህ የጥፋት ሰለባ የሆኑት መከረኞች እየደረሰባቸው ያለው የዘር ማጽዳት ዘመቻ እንዲገታ ተቃውሟቸውን በማሰማት ላይ ናቸው:: ከእኛ የሚጠበቀው የእነዚህ ወገኖቻችንን ስሜት ተጋርተን ጩኸታቸውን አብረን እየጮህን በደላቸው እንዲሰማ የድርሻችንን ማበርከት እንጅ በጥቃት ስሜት እየተንተከተከ ያለውን የሕዝብ እንቅስቃሴ የሚያጠፋ ቀዝቃዛ ውሀ መቸለስ አይደለም::

ኢትዮጵያን ከወያኔ የጭቆና አገዛዝ ነጻ ለማድረግ የሚደረገው ግብግብ በአማሮች ላይ ብቻ የተጣለ ሸክም እንዲሆን የማይፈቅዱ አማሮች መኖራቸውን አምነን መቀበል ከስህተት ያድነናል:: ስለዚህ መተያየት እንዳይፈጠርና ወደኋላ ማለትን እንዳያስከትል በሚተላለፉት መልእክቶች ላይ ጥንቃቄ ሊደረግ

ተገቢ ነው:: የሚሻለው: እንቅስቃሴ በማይታይባቸው አካባቢወች የጸረ-ወያኔው የአመጽ እንቅስቃሴ እንዲጀመር አመቻችቶ ሀገራዊ ገጽታ እንዲላበስ የተቀናጀ ትግል ለማድረግ መጣር ነው::

እንደሚገመተው ከሆነ ዛሬ ላይ የሕዝባቸው ሰቆቃ ያንገፈገፋቸው በብአዴን ውስጥ ያሉ የአማራ ልጆች ከወገናቸው ጋር መስዋእትነትን ለመቀበል ወስነው በጽናት እንደቆሙ ነው:: እኒያ የወያኔን የጥፋት አላማ በአማራ ላይ ሲፈጽሙና ሲያስፈጽሙ የነበሩት የቀድሞ የብአዴን አመራሮች ከታች እየተሳቡ በወጡ እውነተኛ የአማራ ልጆች የተተኩ መሆኑን የሚያሳይ የተግባር እንቅስቃሴ እንዳለ ለመገንዘብ አያዳግትም::

በአማራ ላይ የሚፈጸመው ሰቆቃ ያብቃ ብላችሁ የሕዝባችሁን የትግል እንቅስቃሴ ደግፋችሁ እየታገላችሁ ያላችሁ እናንተ የአማራ ልጆች ብርቱ ጥንቃቄ ልታደርጉ ይገባል:: ወያኔወች በክፋትና በተንኮል የተራቀቁ ናቸው:: ሌት ከቀን የሚያስቡት ጠላት ነው ብለው የፈረጁትን አማራ ከማጥፋት ጎን ለጎን የሕዝቡን አንድነት ሸርሽረው የተቃውሞውን እንቅስቃሴ ማርገብና ለማይጠረቃ የንዋይ ፍላጎታቸው ለብዝበዛ የተመቸ ሜዳ መፍጠር ነው:: የሚደከሙት ለዳር ድንበር መከበርና ለሀገር ብልጽግና: ለህዝብ ሰላም: ፍቅርና አንድነት አይደለም:: እነርሱን የሚያሳስባቸው ከፈረሹበት የእርዝቅ መንበር ላይ የሚቀመጥ የልጅ ልጅ ተከተው ትግራይ-መር ኢትዮጵያን ለማስቀጠል ምን እናድርግ የሚለው ጥያቄ ብቻ ነው::

ይህን እነርሱ በጎ የሚሉትን አላማቸውን ለማደናቀፍ የሚነሳን ማንኛውም አካል ከማጥፋት ወደኋላ አይሉም:: ቂመኞች በመሆናቸው ይቅርታን አያውቁም:: ሸንፈትን አምኖ እንደ እንግዳ ዶሮ አንገትን ቀብሮ ከነርሱ ስር ማደር ከመጠቃት አያድንም:: በህይወት ላሉ አማራወች ይቅርና ለሞቱ አባቶቻችን ያልተኙ መርዘኞች መሆናቸውን ለአፍታም ቢሆን መዘንጋት አያስፈልግም:: የሚሻለው "ከውርደት ሕይወት-የኩራት ሞት!" ይመረጣል ብሎ ከህዝብ ጎን ተሰልፎ እስከመጨረሻው ድረስ እየተፋለሙ ጥሎ መውደቅ ነው:: ነካክቶ ማፈግፈግ የረባ ነገር ሳይሰሩ ቀስ በቀስ ከምድረገጽ መጥፋትን ያስከትላል:: የሚያሸንፉን አንድ ሆነው በአንድ ልብ ስለተሰለፉ እንጅ በምናቸውም ከእኛ ስለሚበልጡ አይደለም:: ልብ አድርጉ! ይህንን የተነቃቃ የህዝብ ትግል እንዲበርድ አድርጎ ማፈግፈጉ ጉዳቱ ቀላል አይሆንም:: በቅንጅት አመራሮች የተሳሳተ አካሄድ የሕዝባችን የትግል መንፈስ የተቀዛቀዘበት ሁኔታ ተከስቶ እንደነበር ማንም አይስተውም:: አሁን ገንፍሎ እየወጣ ያለውን የሕዝብ አመጽ በአግባቡ ካልተጠቀምንበት ጭራሹኑ የተሰበረ መንፈስ ፈጥሮ ዳግም ይህን እድል የማናገኝበት ሁኔታ ሊያስከትል ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው::

ትግሉን ለማቀላጠፍ ዝግጁ ሆኖ መጠበቅ ኋላ ላይ ከመደናበር ያድናል:: ለዚያም ነው እስከቀበሌ ድረስ ወርዶ ሕዝብን የማንቃት: የማደራጀትና የማስታጠቅ ስራ ለይደር የሚተው የማይሆነው:: ስለሀገር አንድነትና ስለሕዝብ ነጻነት የሚጨነቁ ግለሰቦችና ፓርቲወች ድጋፋቸውን እንዲያበረክቱ ለማስቻል በራችሁን ብትከፍቱ የተሻለ ነገር አቅዶ ለመተግበር ይጠቅማል:: እናንተ ለማስተባበር ከቀረጣችሁ ጥሎ ለመውደቅ ፈክሮ የሚነሳው አማራ ድፍን ኢትዮጵያን እንደጉድ ማጥለቅለቁ የማይቀር ነው:: ይህን ለማድረግ ስትነሱ በቅድሚያ ከመሀላችሁ ተሰግስገው ለወያኔ አይንና ጆሮ ሆነው እየሰሩ ያሉትን ባንዳወች በማጽዳት መሆን አለበት::

አማራ ሲፈጥረው በሞራል የተገነባ ሕዝብ ነው:: ከሌላ አካባቢ መጥተው ተመሳስለው ለሚኖሩ ሰዎች ያለው ፍቅርና ክብር የተለየ ነው:: በሆነ ምክንያት ከሌላ አካባቢ ከመጡት ሰዎች ጋር የተጋጨ ያገር ሰው ቢኖር ይወቀሳል:: "የሰው አገር ሰው እንዴት ለማስቀየም ደፈርህ? ከወዳጅ ከዘመድ ርቆ እኛን አምኖ እኛኑ ዘመድ አድርጎ ተጠግቶ የሚኖርን ሰው ማስቀየም ደግ ነው?" ተብሎ ውግዘት ይደርስበታል:: በዚህም የተነሳ በአማራ ክልል የሚኖሩ የሌሎች ክልሎች ኗሪወችም ሆኑ የውጭ ሀገር ሰዎች ከአካባቢው ተወላጅ በተሻለ ሁኔታ ያለሀሳብ ተከብረው በሰላም ይኖራሉ:: ይሁንና "ያልበደለ ሰው ለምን ይቀጣል!" የሚሉ ተቆጭ ሽማግሌወች በሌሉባቸው አካባቢ የሚኖሩ ዘረኞች ከሌላ አካባቢ የመጡ ናቸው በሚሏቸው ምንም ጥፋት በሌላቸው ሰላማዊ አማራወች ላይ አማራ በመሆናቸው ብቻ ሀብታቸውን ይዘርፏቸዋል: ያፈናቅሏቸዋል: አስረው ያሰቃይዋቸዋል: ይገድሏቸዋል:: ይህን ከሞራልና ከሐይማኖታዊ ባህሪይ ያፈነገጠ ወንጀል ሲሰሩ ጠያቂ ሕግ: ወቃሽ ህሊናም ሆነ የሚፈሩት አምላክ የላቸውም:: እንዲህ ያለውን የሕዝብ ሰቆቃ ማስቆም የሚቻለው አንገትን ደፍቶ በመኖር ሳይሆን ግንባር ለግንባር ገጥሞ በመፋለም ነው::

አማራው ከአማራ ክልል ውጭ ሲኖር በየትኛውም ደረጃ በፖለቲካ አመራርነት መሰየም ቀርቶ የግልም ሆነ የሲቭል ስራውን በሰላም ሰርቶ መኖር አልፈቀድለት ብሎ ፍዳ ሲያይ ኖሯል:: በሌላ በኩል በአማራ ክልል የሚኖሩ የሌላ ክልል ተወላጆች በክልሉ የፖለቲካ ሀላፊነት ሳይቀር ከታች እስከላይ ድረስ ተሰግስገው ያለሀሳብ እየፈረዱ እያስፈረዱ ተቀምጠዋል:: በግል ስራ የሚተዳደሩትም ቢሆኑ ከኗሪው በላይ ሆነው ስለያንዳንዱ ግለሰብ መረጃ በማቀበል ሲያሳፍኑና ሲያስገድሉ እስካሁን ድረስ ዘልቀዋል:: በዚህ የተዛባ ተግባራቸው ለማፈር ያልታደሉት እነኂ ሰዎች ይባስ ብለው በአንድ ድምጽ "አህያ: ደደብ: የማይመጥኑ---" ናቸው ብለው የአማሮችን ተግባርና ባህሪ የማይገልጽ የስድብ ስም ሰጥተው አማሮችን በማንቋሸሽ እየጠሯቸው ነው:: ከአሁን በኋላ አማራው ግፍ ተሸክሞ አህያ የሚባልበት

የትግሬ ወያኔወች የሀገር ሀብት እየዘረፉ ብልጥ የሚባሉበት ጊዜ ያበቃል:: ቢችሉ ከብልጥነት ወጥተው ብልህ ለመሆን ቢሞክሩ በዋናነት ለራሳቸው ይጠቅማቸዋል::

አማራ ማንንም በክፉ የሚያይ ሕዝብ አይደለም:: ሌላውም እንደራሱ የሚያስብ መስሎት ለረጅም ጊዜ ለመከራ ተጋልጦ ቆይቷል:: "ሞኝ የዕለቱን ብልህ ያመቱን" እንዲሉ አማሮች የዘላለም ህይወት ለመታደል ለህሊና የማይቆረቁር በፈጣሪ ዘንድ የተወደደ ተግባር በመፈጸም ታጋሽነታቸውን ሲያሳዩ የትግሬ ወያኔወች ግን የአፍታ ህይወት አጓጉቷቸው: ትዕቢት ልቦናቸውን ሰውሮት ከህዝብ ቀምተው ህዝብን እያዋረዱ ጥለውት የሚሄዱት ሀብት ያከማቻሉ:: ከእንግዲህ በኋላ ግን ሁኔታወች መስተካከል ይኖርባቸዋል:: ከቀን ቀን ይማራል የማይባልን አጥፊ ሰው አዝሎ እሹሩሩ ማለት ጉዳት እንጅ ጥቅም የለውም:: አማሮች አሁንም ቢሆን ባለጌወችን ፈርተው ሳይሆን አምላክን ስለሚያስቡ መሰረታዊ ባህሪያቸውን ቀይረው ማንንም ለማጥፋት ወይም ለመበቀል የሚነሱ አይሆንም:: ነገር ግን ከእንግዲህ በኋላ የትግሬ ወያኔወች ከመሀላቸው ዘና ብለው ተቀምጠው መረጃ እያቀበሉ ትግሉን እንዲያከሽፉ: ጭቆናን እንዲያስቀጥሉ  ሊፈቀድላቸው አይገባም:: " የሰው ሞኝ የለውም ብልሀቱ ይለያያል እንጅ!" አይደል የሚባለው? እኛም እንዳቅማችን ብልሀት አናጣም:: ሰላማዊ ኗሪ መስለውም ሆነ በግላጭ የጦር መሳሪያ ታጥቀው የወያኔ የመረጃና የአፋኝ ኃይል ሆነው የሚሰሩ በክልሉ የሚኖሩ ግለሰቦችና ቡድኖች ባስቸኳይ ክልሉን ለቀው እንዲወጡ ይደረግ:: ይህን የሕዝቡን ትግል ለማኮላሸት የተሰገሰገን የጥፋት ኃይል በጉያ ታቅፎ ይዞ ታግለን እናሸንፋለን ማለት ከየዋህነት የዘለለ ሞኝነት ነው:: ይህ የዘረኝነት ጉዳይ አይደለም: መተኪያ የሌለው የትግል ስትራቴጅ እንጅ::

አማሮች አሁንም ኢትዮጵያን ይወዳሉ:: አሁንም የህዝብን በሰላም አብሮ መኖር ይፈልጋሉ:: አይደለም በአንድ ሀገርና በአንድ ሰንደቅ አላማ ስር ክፉና ደጉን ተጋርተው አብረውት ለኖሩ ሕዝቦች ይቅርና ከሌላ ሀገር ለመጣ ሰላማዊ ሰውም ቢሆን ፍቅርና ክብር የሚሰጥ ትሁትና ፈሪሀ-እግዚአብሔር ያደረበት ሕዝብ ነው: አማራ:: ሰላም የሚነሱት ወያኔወች በያዙት መንገድ እስከቀጠሉ ድረስ ግን "ለሰላም ስትሉ ሁሉንም ነገር ተውት" ማለት "በወያኔ የሚደርስባችሁን ግፍ ችላችሁ አንገታችሁን ደፍታችሁ ተቀመጡ" ማለት ነው:: ከእንግዲህ በኋላ በሀገር ልጅነት ስም ነጻነታቸውን ተገፈው በባርነት ለመኖር አይፈቅዱም:: በዚህ ምክንያት የሚደፈርስ ሰላም ካለ መደፍረሱ የግድ ይሆናል:: ሰላም በአንድ ወገን ፍላጎት ብቻ የሚመጣ አይደለም::

ካድሬወቹን በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን እያቀረበ "ጥያቄ ካለ በሰላማዊ መንገድ መጠየቅ ሲቻል ለአመጽ መነሳሳት አግባብ አይደለም" የሚል የማጭበርበሪያ አስተያየት የሚያሰጠው ወያኔ ከስህተቱ ቢማር

ይበጀዋል፡፡ ለሕዝብ ጥያቄ ጆሮ ሰጥቶ የሕዝቡን ፍላጎት ተከትሎ የሚሰራ ቢሆን ኖሮ አሁን እየታየ ያለው አመጽና ውድመት ባልተከሰተም ነበር፡፡ በየአካባቢው የሚደረጉት እንቅስቃሴወች በሙሉ የሕዝብን ጥያቄ አዳምጦ ትክክለኛ ምላሽ ለመስጠት ፍላጎት ባለመኖሩ የተፈጠሩ መሆኑን ማንም አይስተውም፡፡ ሰላማዊ በሆነ መንገድ የሕዝብን ጥያቄ ያቀረቡ የሕዝብ ወኪሎች በእብሪት ስለታፈኑ ነው ተቃውሞው የተቀሰቀሰው፡፡

የትግራይ ሕዝብ "ጥሩውን ጥሩ፡ መጥፎውን መጥፎ" ማለት ማወቅ አለበት፡፡ ከዚያም አልፎ ጥሩውን በመደገፍ መጥፎውን ደግሞ በማውገዝ ከሌሎች ሕዝቦች ጎን ተሰልፎ አጋርነቱን መግለጽና መስዋእትነት መክፈል ይኖርበታል፡፡ ያ ሲሆን ነው መተሳሰብ አለ ማለት የሚቻለው፡፡

ኢትዮጵያውያን ክፉውንና ደጉን ተጋርተን አብረን ኖረናል፡፡ ዛሬም ያንኑ ልማዳችንን ሳንቀይር እንደወቅታዊ ሁኔታው ወይ አብረን እንስቃለን ወይም አብረን እናለቅሳለን፡፡ አንዳችን እየሳቅን ሌላችን የምናለቅስበት አግባብ ግን ሊኖር አይችልም፡፡

ትንሳኤ ለኢትዮጵያ!